የሰ/መ/ቁ. 80464

ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወይራ እንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ

አቶ ወልደሥላሴ ብረቱ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደርና የንግድ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነገር ፈጅ-

አቶ ዮሐንስ ይረስህ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን ክርክር አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው ወይስ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከውል የመነጨን ክስ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ፤ ተጠሪም በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የአሁን ተጠሪ በድምሩ ብር 395,026.55 (ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ሃያ ስድስት ብር ከ55% ሣንቲም) ለአሁን አመልካች ይከፈል በሚል ተወስኖል፡፡

የአሁን ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩላቸው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) እንደተደነገገው ተከሣሽ የሆነው መስሪያ ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት አንዱ በመሆኑ ይህ የአስፈፃሚ አካል የገባውን አስተዳደራዊ ውል በሚመለከት የሚነሣው ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሌለው ስልጣን የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለውም የአሁን አመልካች በዚህ በፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክርና መንስኤ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል በሚለው ሥር የማይሸፈን መሆኑን መሠረት በማድረግ ጠቅሶ ክርክር በማቅረቡ ሲሆን፤ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው መባሉ በህጉ መሠረት መወሰኑን እንጂ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን አያሣይም በማለት የጽሑፍ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክሩን በማስቀደም ያቀረበ ሲሆን፤ ይዘቱም የአሁን ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተወሰነ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት እርሱ በሌለበት ጉዳዩ ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት እንደገና እንዲታይለት ከሚያቀርብ በቀር በቀጥታ የይግባኝ ክርክር የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ በዚህ ከሥነ-ሥርዓቱ ውጭ በሆነ አቀራረብ ውሣኔው መሻሩ የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተመሣሣይ የክርክር ነጥብ ከዚህ ቀደም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 36412 በቀረበው ጉዳይ ላይ በ13/2/01 ዓ.ም. ቀን በዋለው ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 ድንጋጌ ይዘት የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንደ ቋሚ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ አለመሆኑ ይልቁንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 የተመለከተው ሥነ -ሠርዓታዊ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70(ሀ) መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠ ከሆነ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ለመከራከር መብት የሌለው ከመሆኑ በቀር የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከህግ አንፃር እንዲታይለት ይግባኝ የመጠየቅና በይግባኝ የማሰማት መብት ያለው መሆኑ በተብራራ አኳኋን ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም ጉዳይ ያሁን ተጠሪ ያደረገውና ያቀረበው ክርክር ቢኖር ተከሣሽ ቀረበም አልቀረበም አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየትና ለመዳኘት ሥልጣን ያለው በየትኛው ደረጃ የተደራጀ፤ (የተቋቋመ) ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ነጥብ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37፣ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 23(1)(ለ)፣ 244(3) አንፃር ተመልክቶ የጉዳዩ ባለቤት መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ መወሰን የዳኝነት ሥራ ተግባር የሚያስገድደው ሆኖ እያለ ይህንኑ በህግ የተመለከተ የዳኝነት ተግባር አልተወጣም፤ ይህ ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ይታይ በማለት ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐ/ቁ. 329 የተመለከተውን ሥነ- ሥርዓታዊ ድንጋጌ አፈፃፀም የጣሰ መሆኑን አያመለክትም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የአስተዳደር ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132 ላይ በህግ ተለይቶ በተደረገ ጊዜ ነው የሚለውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ብሎ ህግ ተነግሯል የሚባለው ደግሞ በንብረት ህግ አንቀጽ 1444(2)፣ 1446 እና 1447(1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር እጅግ የጠበበ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ የተከተለ የትርጉም መስመር አይደለም ይልቁም በፍ/ህ/ቁ. 3132 እንደተመለከተው አንድ ውል “የአስተዳደር ውል” ነው

በሚለው ማእቀፍ ሥር ይወድቃል ወይስ አይወድቅም ብሎ ለመወሰን መመዘኛ ተደርገው የተያዙት በህግ ወይም በተዋዋዮቹ ግልጽ የሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እነደሆነና፤ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውል አፈፃፀም የአስተዳደር ፍ/ቤቱን ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡ ከእነዚህም መስፈርቶች አንፃር አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ለማለት የግድ በውሉ ላይ በግልጽ መነገር ብቻ ሣይሆን የውሉን ዓይነት የውለታውን ጉዳይ እንዲሁም የተዋዋዮችን ማንነት በማየት መለየት እንደሚገባ በዚሁ ህግ የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የሚለይ እንጂ የአሁን አመልካች ከጠቀሷቸው የንብረት ህግ ድንጋጌዎች አንፃር ብቻ ታይቶ ሊወሰን ይገባል የሚለውን ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡

ከዚህም አንፃር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ከአሁን አመልካች ጋር ውለታ የገባው ማን ነው የሚለውንና የውለታውን ጉዳይ በማየት ውሉ የአስተዳደራዊ ውል ነው፡፡ ይህንኑ አስተዳደራዊ ውልም የገባው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙት አስፈፃሚ አካላት መካከል አንዱ የሆነው ተጠሪ የመሆኑን ፍሬ ጉዳዮች መነሻ አድርጎ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132(ለ) እና በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በአግባቡ ተመልክቶና ተርጉሞ መሆኑን እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 115093 በቀን 12/04/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 76951 በቀን 25/08/2004 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 176341 በቀን 10/10/2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
3. በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የክርክር ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ